ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፪ ፣ ግንቦት ፳፻፲፭ ዓ.ም

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት።



የአለም የአካባቢ ቀን ለአራት ቀናት በአዲስ አበባና በጂጂጋ ከተሞች ተከብሮ ውሏል

በዚህ እትም. . .

የአካባቢ ሪፖርት አቀራረብ አጠቃላይ እይታ ፪

ዜናዎች ፪

ሁነቶች ፬

በስቶክሆልም +50 ብሄራዊ እና አለምአቀፍ ምክክሮች ወቅት የተላለፉ ቁልፍ መልዕክቶች ፫

ልዩ ልዩ ሀትመቶች ፮



ዋና አዘጋጅ፥ ንጉሱ ለማ ገብሬ

አዘጋጆች፥ ተስፋዬ ታሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ እና ሮቢ ረዳ

አምደኞች፥ መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

ግራፊክስና ሌይአውት፥ አርሴማ አንዳርጋቸው

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
Environmental Protection Authority

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፪

ዜናዎች

የዓለም የአካባቢ ቀን በኢትዮጵያ በድምቀት ተከበረ

በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም የሚመራው የዓለም የአካባቢ ቀን እ.አ.አ. ከ1973 ጀምሮ በየአመቱ ግንቦት 28 (ጁን 5) ተከብሮ ይውላል። የዘንድሮ አመት የዓለም የአካባቢ ቀን "አንድ ምድር ብቻ!" በሚል መሪ ሀሳብ በመላው አለም ተከብሯል።

የዓለም አካባቢ ቀን በሀገራችን ለ29ኛ ጊዜ ከግንቦት 26-29 በአዲስ አበባ እና በጅግጅጋ ከተሞች በድምቀት ተከብሯል። በአሉ በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሁነቶችና ልምድ ልውውጦች የተከበረ ሲሆን እነዚህም የዘላቂ አመራረት ስልቶች፣ የአገልግሎት አሰጣጦች እና የቴክኖሎጂ ሽግግርና ተጠቃሚነትን የሚያሳይ ኤግዚቢሽን፣ የፓናል ውይይቶች፣ የድዳት ዘመቻዎች፣ የሩጫ እና የትምህርት ቤት የአካባቢ ክበባት የጥያቄና መልስ ውድድሮችን ያካተቱ ነበሩ።

ስቶክሆልም +50

እ.አ.አ. ከሰኔ 2–3/2022 የስዊድን እና የኬንያ መንግስታት በመተባበር የአለም አካባቢ ፕሮግራም ምስረታን 50ኛ ዓመት የዘከረና ስቶኮሆልም +50 የተሰኘ ከፍተኛ ጉባኤ በስቶክሆልም ከተማ አስተናግደዋል። የስቶክሆልም +50 ጉባኤ ዓላማ አለማችን ወደ ዘላቂ እና አረንጓዴ ልማት የምታደርገውን ሁሉን አቀፍ ሽግግር፣ የተሻለ የስራ እድል አቅርቦትን እና ለሁሉም ሰዎች ምቹ የሆነ አካባቢን እውን ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ለማፋጠን በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ በመምከር ስምምነት ላይ መድረስ ነው።

በምልዐተ ጉባኤው ላይ የሀገራት መሪዎች ጠንካራ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን፣ የስዊድን ጠቅላይ ሚኒስትር "በአረንጓዴ ሽግግር ሂደታችን ውስጥ ማንኛውም አገር ወደኋላ እንዳይቀር ማረጋገጥ አለብን፤ ይህንን ማድረግ ደግሞ አማራጭ ብቻ ሳይሆን የሞራል ግዴታችንም ነው" በማለት ጥሪ አቅርበዋል። የኬንያው ፕሬዝዳንት ኡሁሩ ኬንያታ በበኩላቸው "ወደ COP 27 በምንሄድበት ጊዜ ሁሉን አቀፍ፣ ሁለንተናዊ እና ለውጥ አምጪ የአካባቢ ጥበቃ እርምጃዎችን ይዘን መሆን ይኖርበታል" ብለዋል።

የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የተከበሩ ዶ/ር ዐብይ አህመድን ጨምሮ የበርካታ ሀገራት መሪዎች በምስልና በድምፅ የተቀረፀ መልእክቶቻቸውን የላኩ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትራችን በመልዕክታቸው "ሁላችንም ለአካባቢ ጥበቃ ተግባራት መተባበር እና አካባቢያዊ ተግዳሮቶችንም በጋራ ጥረታችን ለመቅረፍ መዘጋጀት ይኖርብናል" ብለዋል። በመቀጠልም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በቅርበት እየሰራች ባለው የአረንጓዴ አሻራ ልማት በቀጣይም በቁርጠኝነት እንደምትቀጥል አረጋግጠዋል።

በጉባኤው ከምልአተ ጉባኤው መድረክ በተጨማሪ የአመራር ውይይቶች፣ የጎንዮሽ ምክክሮችና የአህጉራትና የባለድርሻ አካላት ምክክር ተካሂዷል።

የአካባቢ ሪፖርት አቀራረብ አጠቃላይ እይታ

- አንተነህ ተሾመ፤ በኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ጥበቃና ሪፖርት ዘገባ ዳይሬክተር ጀነራል

የአካባቢ ሁኔታ ሪፖርት ምንድን ነው?

እ.አ.አ. ከ1960ዎቹ በፊት፣ የአካባቢ ሁኔታ ሪፖርቶች አልነበሩም። አሜሪካ እና ጃፓን በ1970ዎቹ መጀመሪያ የአካባቢ ጥራት ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ግንባር ቀደም ናቸው። እ.ኤ.አ. በ1992 በሪዮ ከተካሄደው የምድር ስብሰባ በኋላ የአለም ሀገራት መደበኛ የአካባቢ ሪፖርቶችን ለማዘጋጀት ተስማሙ። የአካባቢ ሪፖርት አስቀድሞ የተገለጸን ጂኦግራፊያዊ አካባቢን (ለምሳሌ ብሔራዊ ወይም ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት) የሚሸፍን ሲሆን የተፈጥሮ አካባቢን (ባዮ-ፊዚካልን) ያቀፈ፣ የአካባቢ ሥርዓትንና የአካባቢን ሁኔታ እና አዝማሚያ የሚገልጽ ሰነድ ነው። የአካባቢ ሪፖርቶች በተለያዩ የአካባቢ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ወቅታዊ፣ ትክክለኛ፣ ተአማኒ እና ጠቃሚ መረጃዎችን ለማመንጨት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ስለዚህ ለዘላቂ ልማት አስተዳደር የሚረዳ ውሳኔዎችን ያሳውቃል ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ውሳኔዎች በአካባቢው ላይ የሚያመጡትን ተፅእኖ ይለካል።

የአካባቢ ሪፖርት በራሱ ፍጻሜ እንዳልሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። ትክክለኛ እና ጠቃሚ መረጃን ለትክክለኛዎቹ ተጠቃሚዎች በማቅረብ እና ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ በማድረግ ዘላቂ የሀብት አስተዳደርን ለማሳካት የታለመ ሰፊ ሂደት አካል ነው። ስለዚህ፤ የአካባቢ ሪፖርት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች፣ በዘላቂ ልማት ውጤታማ ትግበራ እና በፖሊሲ ቀረጻ ላይ እንደ መሳሪያነት ያገለግላል።

የአካባቢ ሪፖርት ቀደም ባሉት ጊዜያት በአካባቢያዊ ሁኔታዎች እና አዝማሚያዎች ላይ መረጃን ስልታዊ በሆነ መንገድ ማግኛ፣ መተንተኛና እና ማቅረቢያ መንገድ ነበር። የቀድሞ የአካባቢ ሪፖርት ዋና ጭብጥ በሰዎች ተግባራት፣ በተፈጥሮ ሂደቶች እና በአካባቢ ሁኔታዎች መካከል ያለው ትስስር ማሳየት ነበር። ነገር ግን፣ የሪፖርት አቀራረብ ስልቱ ከአዝማሚያዎች እና ሁኔታዎች ወደ

ወደ ገፅ ፫

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፪

ከገፅ ፪ የቀጠለ

ትንተና ሲሸጋገር፣ እነዚህን ከዋና ዋና መንስዔዎች እና ፖሊሲዎች ግምገማ ጋር በማዋሃድ ተለይተው የታወቁትን የአካባቢያዊ አዝማሚያዎች የሚያስከትሉትን ወይም ተጽዕኖ የሚያሳድሩትን መለየት አስፈላጊ ነው። ይህ አካሄድ የተቀናጀ የአካባቢ ምዘና እና ሪፖርት (IEAR) በመባል ይታወቃል፤ ይህም በቀላሉ "በተፈጥሮ አካባቢ እና በህብረተሰብ መካከል ባሉ ቁልፍ ግንኙነቶች ላይ ከፖሊሲ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎች የማዘጋጀት እና የማስተላለፍ ሂደት" ተብሎ ይገለጻል።

ለምን የአካባቢ ሁኔታ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት አስፈለገ?

የአካባቢ ሪፖርቶች በአንድ ሀገር ውስጥ አካባቢ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን፣ አዝማሚያዎችን እና ቁልፍ መንስዔዎችን እና ፖሊሲዎችን ለማወቅ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪ እንደ የአካባቢ ትምህርት እና የህዝብ ግንዛቤ ምንጭነት ያገለግላሉ። በዋናነት የሚዘጋጀው ህዝቡን እና ፖሊሲ አውጪዎችን ከአካባቢያዊ የጥራት አመልካቾች ጋር ለማስተሳሰር ሲሆን ይህም ማህበረሰቡ የራሱ ድርቶች የሚያስከትሉትን አሉታዊ ውጤቶች እንዲያስተውል ሲረዳ፣ ፖሊሲ አውጪው ደግሞ ምን እና የት መተግበር እንዳለበት እንዲገነዘብ ያደርጋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀው ሪፖርት የአካባቢ መረጃን በማሰባሰብ ደረጃ እና ሁሉን አቀፍ መሆን ስለሚያስፈልገው እንደ በኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ላሉ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን/ወረዳና ቀበሌ ጠቃሚ አይደለም። ስለዚህ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአካቢቢ ሪፖርት፣ የአካባቢ ጉዳዮችን በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ልማት ሂደት ውስጥ ማካተትን ጨምሮ ውሳኔ ሰጪዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች እና ሕዝቡ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት በጣም ጠቃሚ መሣሪያ ነው።

የብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ሪፖርቶች ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ በክልሎች መካከል ጤንካራ የተወዳዳሪነት መሳሪያ ሊሆን ይችላል። ንፁህ አካባቢ፣ በቂ መሠረተ ልማት እና ምክንያታዊ የታክስ ሥርዓት ያለው ክልል፣ ደካማ መሠረተ ልማት ካለው የበለጠ የግል ኢንቬስትመንትን ሊስብ ይችላል። በአጠቃላይ ንፁህ የሆነ አካባቢ የግል ካፒታልን በመሳብ ረገድ ከሌሎች የበለጠ ዕድል ይኖረዋል።

የአካባቢ ሪፖርት የአየር እና የአየር ንብረት ለውጥን፣ መሬትን፣ የውሃ ሃብትን፣ ደንና ብዝሃ ህይወትን በሚመለከት የአካባቢ ሁኔታ ላይ ትንታኔዎችን ያቀርባል። እንደ ሥርዓተ-ፆታ እና አካባቢ፣ አካባቢ እና ጤና እና የቆሻሻ አወጋገድ የመሳሰሉ የፖሊሲ ትንተና እና ተሻጋሪ ጉዳዮችን ያካትታል።

የመንስዔየዎች-ግፊት-ሁኔታ-ተፅእኖ-ምላሽ መዋቅር

የመንስዔየዎች-ግፊት-ሁኔታ-ተፅእኖ-ምላሽ መዋቅር (Driver-Pressure-State-Impact-Response Framework) የማህበረ-ሥነ-ምህዳራዊ ሥርዓቶችን ሪፖርት ለማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ማዕቀፍ ነው። ይህ ማዕቀፍ አገር አቀፍ ደረጃ ግምገማ ለማድረግ ምቹ ነው።

በማዕቀፉ ውስጥ መንስዔዎች በህብረተሰብ እና በአካባቢ መካከል ያለው መስተጋብር ውጤቶች የሆነውን የአካባቢ ሁኔታ አመልካች ናቸው። አገሪቱ/ክልሉ እየሠራበት ያለውን ነባራዊ ሁኔታና እነዚህም በአካባቢ ላይ ምን ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ያብራራሉ። እነዚህም ኢኮኖሚክስ እና የፖሊሲ እና የስነ-ሕዝብ አወቃቀርን ያካትታሉ። ግፊት ሰዎች በአካባቢ ላይ የሚያሳድሯቸው ተጽእኖዎች ሲሆኑ በካይ ልቀቶች እና ብክነትን ያካትታል። እነዚህም የአካባቢን ሁኔታዎች (አካላዊ፣ ኬሚካላዊ እና ባዮሎጂካል) ያስከትላሉ። እነዚህ በምላሹ በሥነ-ምህዳር፣ በሰው ጤና እና በትግበራ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ፣ በመጨረሻም ወደ ፖለቲካዊ ምላሾች ይመራሉ።

ይህ መዋቅር በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ውስጥ በብዙ የአካባቢ ሪፖርቶች አጻጻፍ ሂደቶች ውስጥ በሰፊው ጥቅም ላይ ይውላል።

የኢትዮጵያ የአካባቢ ሁኔታ ሪፖርቶች

ኢትዮጵያ እ.አ.አ. ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የአካባቢ ሁኔታ ሪፖርቶችን ስታዘጋጅ ቆይታለች። ሪፖርቱን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የማዘጋጀት ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነው።

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እ.አ.አ. በ2021 "ለኢትዮጵያ ማህበረሰብ የተሻለ የአካባቢ መረጃን ለማድረስ እንዲሁም

ወደ ገፅ ፬

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፪

ሁነቶች

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መስፋፋት መቀጠሉን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ በበይነ መረብ መካሄዳቸውን ቀጥለዋል። የሚከተሉት ሁነቶች ለማናቸውም ታዳሚዎች ተደራሽ ናቸው። እያንዳንዱን ሁነቶች አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ‹ምንጭ› የሚለውን ማስፈንጠሪያ ይክፈቱት።

- የውሃ ኤሌክትሮሊስስ እንደ አረንጓዴ የሀይል ምንጭ፤ ቀጣይ ሁኔታዎች፣ የታዳሽ ሀይልና እና ሃብት ኢንስቲትዩት፣ እ.አ.አ ሰኔ 2022 | ምንጭ
- የ2022 የአየር ንብረት ፈጠራ መድረክ፤ ክላይሜት አክሽን፣ እ.አ.አ ሰኔ 2022 | ምንጭ
- የአፍሪካ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ኮንፈረንስ፤ ፈጠራ የታከለባቸው ቀጣይ ተፈጥሮአዊ-አዎንታዊ የፈጠራ እርምጃዎች ከፖሊሲ፣ ቢዝነስ እና ፋይናንስ አኳያ ፣ እ.አ.አ ሰኔ 2022 | ምንጭ
- የ2022 የአየር ንብረት ሳምንት፤ አለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ እና ዘላቂነት ኮንፈረንስ፣ የክላይሜት ሊንክስ፣ እ.አ.አ ነሐሴ 2022 | ምንጭ
- የ2022 አለም አቀፍ የውሃ ሳምንት፣ የስቶክሆልም ዓለም አቀፍ የውሃ ተቋም፣ እ.አ.አ ነሐሴ 2022 | ምንጭ
- የ2022 የአለም የውሃ ኮንግረስ እና አውደ ርዕይ፣ የአለም አቀፍ የውሃ ማህበር፣ እ.አ.አ መስከረም 2022 | ምንጭ
- የ2022 አይበገሬ ከተሞች፤ አይ.ሲ.ኤል.ኢ.አይ፣ እ.አ.አ ጥቅምት 2022 | ምንጭ
- የ2022 የካይሮ የውሃ ሳምንት፤ የግብፅ የውሃ ሃብት እና የመስኖ ሚኒስቴር፣ እ.አ.አ ጥቅምት 2022 |ምንጭ

ከገፅ ፫ የቀጠለ

የፌዴራል እና የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት እና የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ መረጃን ለውሳኔ አሰጣጥ እና ዘላቂ የሰው ልጅ ልማት የድርጊት መርሃ ግብርን ለመንደፍ የመጠቀም አቅማቸውን ለማሳደግ" በሚል ራዕይ በአዲስ መልክ ተደራጅቷል።

በኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ ሶስት የሀገር አቀፍ የአካባቢ ሁኔታ ሪፖርቶች (እ.አ.አ. በ2003፣ 2008 እና 2017) እንዲሁም አንድ የክልል እና ከተማ አስተዳደር ሪፖርት በ2015 ተዘጋጅተዋል።

የኢትዮጵያ 3ኛ ብሔራዊ የአካባቢ ሁኔታ ሪፖርት

የመጨረሻው የአካባቢ ሁኔታ ሪፖርት የተዘጋጀው እ.አ.አ. በ2017 ሲሆን በወቅቱ የአካባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን (የአሁኑ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን) የአካባቢን ሁኔታ በመደበኛነት የመገምገም እና ለፖሊሲ አውጪዎች እና ለህዝብ አጠቃላይ ተጨባጭ መረጃ ለማቅረብ በተሰጠው ሃላፊነት መሰረት የተዘጋጀ ነበር። ሪፖርቱ ከላይ የተጠቀሰውን መዋቅር የተጠቀመ ሲሆን ለወደፊቱ ጥሩ መሰረት የጣለና ሰፊ እና ጥልቀት ያላቸው ጉዳዮችን ሸፍኗል።

ሪፖርቱ የአየር፣ የመሬት፣ የውሃ ሃብት፣ ደን፣ ብዝሃ ህይወት እና የአየር ንብረት ለውጥን በሚመለከቱ የአካባቢ ሁኔታዎች ላይ ትንታኔዎችን አቅርቧል። እንደ ሥርዓተ-ፆታ እና አካባቢ፣ አካባቢ እና ጤና እና የቆሻሻ አወጋገድ የመሰሰሉ የፖሊሲ ትንተና እና ተሻጋሪ ጉዳዮችን አካቷል። የሚቀጥለው ሪፖርት በዚህ አመት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፪

በስቶክሆልም +50 ብሄራዊ እና አለምአቀፍ ምክክሮች ወቅት የተላለፉ ቁልፍ መልዕክቶች

❑ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ስቶክሆልም +50 ብሔራዊ ምክክር

ግንቦት 2014 ከተካሄደው የስቶክሆልም+50 አለም አቀፍ ኮንፈረንስ በፊት፣ ኢትዮጵያ ሁለት ሀገር አቀፍ በአካል እና ቨርቹዋል የተካሄዱ የምክክር መድረኮች በአዲስ አበባ ከሚያዚያ 2–3 እና ከግንቦት 4–5 ቀን 2014 አዘጋጅታለች። ዝግጅቶቹ ያተኮሩት በአለም አቀፍ የስቶክሆልም +50 አዘጋጆች በተመረጡት የአመራር የውይይት ጭብጦች ላይ እና በብሔራዊ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ነበር።

ዝግጅቶቹ ኢትዮጵያ ባለፉት 50 ዓመታት የአካባቢ ጉዳዮችን ከልማት አጀንዳዋ ጋር በማዋሃድና በመተግበር ረገድ ያሳየቸውን ጥረት አሳይትዋል። በትግበራው ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና እድሎች የተለዩ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የዘላቂ ልማት ግቦች (SDGs) ትግበራን ለማፋጠንና አጋርነትን ለማስፋት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ተካሂዷል።

በምክክሩ ወቅት በአገር አቀፍ ደረጃ ቅድሚያ የተሰጣቸው አራት ጭብጦች ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን እነዚህም ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚረዱ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች (NbS)፣ የአካባቢ ብክለት እና የኢትዮጵያ ምላሾች፣ በኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃን የሚደግፉ ፖሊሲዎች፣ ተቋማት እና የህግ ማዕቀፎች፣ እንዲሁም የእውቀት አስተዳደር እና ግንኙነት ናቸው።

ሀገራዊ ምክክሩ ኢትዮጵያ ልማቷን ለማሳለጥ ከፍተኛ የስነ-ህይወታዊ፣ ስነ-ምህዳር እና የባህል ብዝሃነት እንዳላት አሳይቷል። ለረጅም ጊዜ የተተገበሩና ወደ ሌላ አካባቢ እንደ መልካም ተሞክሮ መስፋት የሚችሉ አንዳንድ ባህላዊ ልምዶችም ቀርበዋል። ውይይቶቹ ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ ያፀደቀቻቸው የተለያዩ የአካባቢ ጥበቃ ስምምነቶች እና በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ዘርፎች የወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎችን ያካተቱ ነበር።

ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች ለመተግበር ካጋጠሙ እክሎች ውስጥ የደን መጨፍጨፍ፣ የደን መመናመን፣ የአፈር መሸርሸር፣ የብዝሀ ህይወት መጥፋት፣ ብክለት፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና ያልተደራጀ የቆሻሻ አወጋገድ ይገኙበታል። እነዚህ ተግዳሮቶች በቴክኒክ፣ በገንዘብና በማህበራዊ ችግሮች፣ ለተለያዩ ተቋማት በሚሰጥ ተደራራቢ ኃላፊነት እና በባለድርሻ አካላት ትብብርና ቅንጅት ደካማነት እየተባባሱ መሆናቸው ተጠቁሟል።

የተጠቆሙት ዋና ዋና የመፍትሔ ሃሳቦች ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች፣ ቁሳቁሶችን መልሶ ወደጥቅም ማዋልን ጨምሮ ፈጠራ የታከለበት የቆሻሻ አወጋገድ፣ ትብብር እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ እውቀትን በጋራ ማፍለቅ እና የምርምር ውጤት አሰራጭ አካላትን አቅም መገንባታ ይገኙበታል።

በሀገር አቀፍ ምክክሩ ወቅት ሶስት የአመራር ውይይቶችም የተካሄዱ ሲሆን እነዚህም፤

የአመራር ውይይት 1፡ ጤናማ ፕላኔት እና የሁሉንም ብልጽግና ለማረጋገጥ በፍጥነት ወደ ትግበራ መግባት

ተፈጥሮን ወደነበረበት መመለስ እና ማደስ ህብረተሰቡን በኢኮኖሚም ያሳድጋል። ኢትዮጵያ በእርሻ-ሥነ-ምህዳር፣ በብዝሀ ሕይወት (ሥነ-ምህዳር፣ ዝርያ፣ እና የዘረመል ብዝሃነት) እና በተለያዩ ባህሎች የበለፀገች በመሆኗ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ጥሩ ዕድል አላት። በሁምቦ የሚገኘው ተፈጥሮን በራሱ እንዲያገግም የማገዝ ፕሮግራም፣ የጌዲኦ ባህላዊ የእርሻና ደን ልማት እና የኮንሶ ባህላዊ የእርከንና የዛፍ ተከላን ጨምሮ በስፋት ቢተገበሩ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ በርካታ ምርጥ ተሞክሮዎች የቀረቡ ሲሆን እነዚህን አሠራሮች ማስፋፋት በርካታ ቅድመ ተግባራትን እና የአጋሮችን የተቀናጀ ጥረትን እንደሚጠይቅ ተገለጿል።

የአመራር ውይይት 2፡ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ዘላቂ እና ሁሉን ያካተተ ማገገምን ማሳካት

የሚከተሉትን ጨምሮ በመንግስት፣ በግል እና በሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች የተለያዩ ዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ የማገገሚያ ልማዶች በመተግበር ላይ ናቸው።

ወደ ገፅ ፯

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፪

ልዩ ልዩ ሀትመቶች

በኢትዮጵያ በተለያዩ ከፍታዎች ላይ በሚገኙ የሰብል ምርቶች ላይ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው የተለያዩ ተፅዕኖዎች


ይህ ጥናት እንደሚያመለክተው በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የተለያየ ከፍታ ባላቸው ቦታዎች ላይ የተዘሩ የሰብል ምርቶች የምርታማነት መጨመር ወይም መቀነስን ያሳያሉ። ጥናቱ የግብርና ልማት መርሃ ግብሮች እና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ስልቶች የአካባቢ ሁኔታን እና የሰብል ምርቶች ለአየር ንብረት ለውጥ ያላቸውን የመቋቋም አቅምን ያገናዘቡ እንዲሆኑ በማድረግ የአነስተኛ አርሶ አደሮችን የአየር ንብረት ለውጥ የመቋቋም አቅምን እና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል እንደሚቻል ይመክራል። ምንጭ

የፕላስቲክ ብክለት በአፍሪካ



ይህ ሪፖርት በአፍሪካ የፕላስቲክ ብክለት ሁኔታ እና ተፅእኖን የሚዳስስ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነ ዘገባ ሲሆን ከነባር የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎች ጋር ተዳምሮ የመስኩን ተግዳሮቶች ለመፍታት በሚያስፈልጉ የፖሊሲ አማራጮች ላይ የውሳኔ ሃሳቦችን በአስቸኳይ፣ ሁሉን አቀፍ በሆነ እና በተቀናጀ አኳኋን የሚያመላክት ነው። ምንጭ

የአየር ንብረት ለውጥ 2022፣ የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ



ስድስተኛ የመንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ስብስብ (IPCC) የአየር ንብረት ማስተሰሪያ ሪፖርት፣ በአለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ማስተሰርያ እንቅስቃሴዎች እና ቃልኪዳኖች የአፈጽጸም ሁኔታን እና የልቀት ምንጮችን መርምሯል። ዘገባው በማከልም የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ከመቀነስ ረገድ የሀገራትን ጥረቶችና የሚስተዋሉ ለውጦችን ከረጅም ጊዜ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ለመቀነስ በሀገራት ከተወጠኑ የእቅድ ግቦች አኳያ ገምግሟል። ምንጭ

ከገፅ ፭ የቀጠለ

- ባህላዊ የማህበረሰብ ራስን መደገፍ ስርዓቶች፤ ኢትዮጵያውያን የጠነከረ የቤተሰብና የማህበረሰብ ትስስር፣ ጠንካራ ማህበራዊ ካፒታል እና የመተጋገዝና የመተሳሰብ ባህል አላቸው። ኮቪድ-19ን ተከትሎ መንግስት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እነዚህ ማህበራዊ አውታረ መረቦች በመጠቀም ለተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎች የሀብት ማሰባሰብያ ዘዴን ነድፈዋል። በተጨማሪ የመከላከያ ቁሳቁሶችን ጭንብል፣ እጅን ማዝጃዎች እና ክትባቶችን ለህዝብ ሲያቀርቡ ቆይተዋል።
- መንግስት ወረርሽኙ በታይለኛ በተከሰተበት ወቅት ድርጅቶች በከፊል እንዲዘጉ ያዘዘ ሲሆን፣ ይህም ማለት ከቤት ሆነው መሥራት የሚችሉት ይህን ማድረግ ሲችሉ፣ አስፈላጊዎቹን የኮቪድ-19 የጥንቃቄ መንገዶችን ጠብቀው ሌሎች ወደ ሥራ ቦታ እንዲሄዱ ያስቻለ ነበር። ይህም በቀን ገቢ የሚተዳደሩ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች በከባድ ሁኔታ እንዳይጎዱ ረድቷል።

የአመራር ውይይት 3፡ በዘላቂ ልማት አካባቢዊ ጉዳዮችን ተግባራዊ ማድረግ

በአለምአቀፍ ደረጃ ሶስት የአለማችንን ቀውሶች (የአየር ንብረት ለውጥ፣ ብክለት እና የብዝሀ ህይወት መጥፋት) እና የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለማሸነፍ የሚደከምበት ወቅት ላይ እንገኛለን። የማይመለሱ ጥፋቶችን ለማስወገድ እና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት የተፋጠነ እርምጃ ያስፈልጋል። ለ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን እና ሌሎች ለአካባቢ ጥበቃ ቃል የገባናቸውን እቅዶች በተግባር ላይ ለማዋል በአለም አቀፍ ደረጃ እያጋጠሙን ያሉ ፈተናዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

- ባደጉ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት መካከል ጠንካራ ትብብር እና አጋርነት አለመኖር።
- በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ውስጥ ያለው ደካማ ኢኮኖሚ እና የቴክኒክ አቅም አለመኖር ለአለማችን ቀውሶች እና ከኮቪድ-19 ለማገገም የበኩላቸውን ሚና ለመጫወት እንቅፋት መሆናቸው።
- በታያላን ሀገራት መካከል የሚታዩ የሃሳብ ልዩነት እና በአለም ላይ በተከሰቱት የትጥቅ ግጭቶች መስፋፋት ምክንያት አለም አቀፍ ትብብሮች መቀነሳቸው።

ወደ ገፅ ፮

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
Environmental Protection Authority

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፪

ከገፅ ፮ የቀጠለ

ምክረ-ሀሳቦች

- የታዳጊው ዓለም ፍትሃዊ ውክልና ያላቸው ጠንካራ የባለብዙ ወገን ተቋማትን መፍጠር።
- ግልፅ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን እና የተጠናከሩ ተቋማትን በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ መፍጠር።

መልካም ተሞክሮዎችን በማጎልበት የአካባቢ ጥበቃን የተመለከቱ የዘላቂ ልማት ግቦችን ትግበራ ማፋጠን እንደሚቻል መግባባት ላይ ተደርሷል።

የስቶክሆልም+50 ዓለም አቀፍ ስብሰባ

የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ "ስቶክሆልም+50፡ ጤናማ ፕላኔት ለሁሉም ብልጽግና - ሀላፊነታችን፣ ዕድላችን" በሚል መሪ ቃል በስቶክሆልም ከግንቦት 25-26 2014 ዓ.ም. አለም አቀፍ ስብሰባ አካሂዷል።

በስቶክሆልም +50 የ2030 አጀንዳ እና የዘላቂ ልማት ግቦች ትግበራን ለማፋጠን ቁርጠኝነት የተሞላበት የአካባቢ ጥበቃ ርምጃ እንዲወስድ መሪዎቹ ጥሪ ያቀረቡባቸው አራት የምልአተ ጉባኤ ስብሰባዎች ተካሂደዋል። ለሁለት ቀናት በተካሄደው አለም አቀፍ ስብሰባ ሶስት የአመራር ውይይቶች፣ በርካታ በወጣቶች የሚመሩ ክፍለ ጊዜዎችን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ የጎዮሽ ፕሮግራሞች (side events) እና በኢንተርኔት የታገዙ ውይይቶች (webinars) ተካሂደዋል።

ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት የተካሄዱ ተከታታይ ሀገራዊ የባለድርሻ አካላት ምክክሮች በሺዎች የሚቆጠሩ በአለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ውይይቶች እንዲያደርጉ እና ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ አስችሏቸዋል። የሀገራት መግለጫዎች (የኢትዮጵያን ጨምሮ) በተቀረጹ ቪዲዮዎች ቀርበዋል።

የ50 ሀገራት ብሄራዊ ምክክሮች ዋና ዋና ሀሳቦችና ማጠቃለያዎች

- የተሻሻሉ አቅሞች፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የሰሜን-ደቡብ እና ደቡብ-ደቡብ ትብብርን ጨምሮ በአስርተ ዓመታት የትግበራ ወቅት ጠንካራ ትብብር እንዲደረግ ሀገራት ጠይቀዋል።
- የተጠናከረ የአካባቢ አስተዳደር በየደረጃው የሚስፈልግ ሲሆን እነዚህም የተሻሻለ የህዝብ ተሳትፎና የአካባቢ መረጃ ተደራሽነት፣ የተሻሻለ የማስረጃ-መሠረት እና በአደጋ ዙሪያ ዝግጁነት፣ በመንግስታት እና በህብረተሰብ መካከል መተማመንን መገንባት፣ እና ለሴቶች፣ ወጣቶች፣ ለአካባቢ ማህበረሰቦች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ፍላጎቶች ውጤታማ ምላሽ መስጠትን ይጨምራሉ።
- የአካባቢ ፋይናንስ ምንጮችን ማለትም፣ የሀገር ውስጥ እና የአለምአቀፍ ፣የህዝብ እና የግል እንዲሁም ከሁለቱ የተዳቀሉትን በሙሉ በማጠናከር እና ይበልጥ ውጤታማ የሆኑ የአካባቢ እና የአየር ንብረት ፋይናንስ አያያዝን በመተግበር አካባቢ ጥበቃ ላይ ያተኮሩ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ጥሪ ቀርቧል።
- አገሮች ወደ አረንጓዴ እና ጤናማ የልማት ሽግግር ለማድረግ ጠንካራ ድጋፎችን ይፈልጋሉ። ይህም ሀገራዊ ግቦችን እና መለኪያዎችን ለማስተካከል፣ የኢኮኖሚ ስርዓቶችን እና የኢንቨስትመንት ፍሰቶችን ወደ ዘላቂ ፍጆታ እና ምርታማነት ለመምራት እንዲሁም ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የምግብ ፣ የሃይል ፣ የቱሪዝም ፣ የትራንስፖርት እና የመሠረተ ልማት ዘርፎችን የአካባቢ ተፅዕኖ ለመቀነስ ድጋፍ ማድረግን ያጠቃልላል ።
- በስቶክሆልም+50 የአመራር ውይይት ጭብጦች ላይ ሃሳባቸውን በማጋራት በሁሉም ደጋፊ አገሮች የሚገኙ የወጣቶች መሪዎች እና አክቲቪስቶች አስተዋፅኦ አድርገዋል። የወጣቶች ተሳታፊዎች የአካባቢና የአየር ንብረት ትምህርት፣ ስልጠና፣ የአቅም ግንባታ እና የመረጃ ተደራሽነትን አስፈላጊነት ጠቁመዋል። የመንግስታት አረንጓዴ ስራዎችን፣ አረንጓዴ ንግዶችን እና የወጣት ፈጠራዎችን ማስተዋወቅ ያለውን ጠቀሜታ እንዲሁም ለተፋጠነ የአካባቢ እና የአየር ንብረት እርምጃዎች ትግበራ የተጠናከረ ዓለም አቀፋዊ እና ብሔራዊ የገንዘብ ፍሰት አስፈላጊነት ላይ አፅንኦት ሰጥተዋል።

በስብሰባው ተባባሪ አዘጋጆች ስዊድን እና ኬንያ የስብሰባውን የምልአተ ጉባኤ እና የአመራር ውይይቶች ውጤቶችን መሰረት ያደረገ መግለጫ በመስጠት ዝግጅቱ ተጠናቋል። በመግለጫው የሰው ልጅን ደህንነት ማእከል ያደረገ ጤናማ አለም እና አካታች ብልጽግና፣ ንፁህ፣ ጤናማ እና ዘላቂ አካባቢ የማግኘት መብትን ተግባራዊ ማድረግ፤ አሁን ባለው የኢኮኖሚ ሥርዓት ላይ ሥርዓታዊ ለውጦችን ማድረግ እና ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ዘርፎችን እድገት ማፋጠን እንደሚስፈልግ ተገልፅዋል።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዲሪ የአካባቢጥበቃ ባለስልጣን

ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150

ኢሜል: eenvironment@gmail.com;

ድረ ገፅ: https://www.epa.gov.et/

ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም። በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም።

ስራውን የደገፉ አካላት

Climate & Development Knowledge Network

SOUTH SOUTH NORTH
TOWARDS CLIMATE RESILIENCE

Funded by

Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands

IDRC · CRDI
International Development Research Centre
Centre de recherches pour le développement international

Canada

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.

.